# ስለኢትዮጵያ ሰላም፥

## ባለፉት ዓመታት የፈጸምነውን፡
## የጾምና የጸሎት ልዩ ሱባኤ፥
## በዘንድሮዋም የ፪ሺ፲ ዓመተ ምሕረቷ ጳጉሜ፡
## ልናደርግ፥ እነሆ ተዘጋጅተናል!

---

### መቅድም

እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ "ሰላም ለኢትዮጵያ" ኅዋ ሰሌዳ፡ በ፲፱፻፺፱ ዓ. ም ባሳሰበው መሠረት፡ የጾመ ኢትዮጵያን ሥርዓተ ጸሎት ተከትለን፥ ባለፉት ዓመታት፥ የጳጉሜን ዕለታት፡ በያለንበት፡ የጾምና የምጽዋት፥ የጸሎትና የስግደት ሱባኤያዊ ምግባራችንን በማካኼድ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት፡ ሃይማኖታዊ ተልእኳችንን መፈጸማችን ይታወሳል፡፡

ታዲያ! እንዲያ ባለው፡ በተሟላው፡ ሥጋዊ፥ ነፍሳዊና መንፈሳዊ ትጥቃችን ተሰልፈን፡ በተጨማሪ፡ የፀረ ኢትዮጵያዊነትን የኃይል ጥቃት መክተን በመቋቋም፡ የተከናወነው፡ ያ፡ የዓመቱ ተጋድሏችን፡ ተፈላጊውን መልካም ፍሬ በማስገኘት፡ ተሟልቶ መፈጸሙንና በእኛ አሸናፊነት ማብቃቱን የተገነዘቡ የቅርብና የሩቅ ሰብአውያን ወገኖቻችን፥ ዛሬስ ስንቶች ይኾኑ? በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታዊና ምግባራዊ ኃይል የተገኘውን፥ ይህን መልካም ፍሬ፡ እያንዳንዳችን ብናውቀውም፡ ለሌሎች የማሳወቅ ግዳጅ እንዳለብን ደግሞ፥ እናምንበታለን።

ይህን የድምዳሜ አሳብ መሠረት በማድረግ፥ እውነታውን፡ ለሌሎች ለመግለጽና ለማስጨበጥ ስንል፡ ከላይ ለተጠቀሰው ጥያቄ ስንሰጥ የቆየነውን መልስ፡ ከዚህ እንደሚከተለው፡ አብራርተንና አስፋፍተን አቅርበነዋል። ስናቀርበውም፥ እንዲሁ ዝም ብለን አይደለም።

በአንድ ወገን፡ የዛሬውን የኢትዮጵያ ትውልድ በሚመለከት፡ በኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና መካከል፡ እየተካረረ የኼደው መቃቃርና መወጋገዝ፥ ጥላቻና ፀብ፥ በሌላው ወገን ደግሞ፡ “Democracy” በሚባለው ሰብኣዊ ይትበሃል ሽፋን፡ ሥልጣናቸውን፡ በየተወሰኑ አገሮች ኾነ በመላው ዓለም ዘርግተው ባሰፈኑት የሰዎች መንግሥታት የበላይ መሪነት በሚካኼደው ሥልታዊ የአገዛዝ ምርጫ ምክንያት፡ በዓለሙ ሕዝቦች ላይ እየደረሰ ያለውን ጠንቀኛ ችግር እየጠቃቀስን በማውሳት ጭምር ነው እንጂ።

ይህም፡ "ጦርነትን፥ የጦርነትንም ወሬ ትሰሙ ዘንድ አላችሁ፤ ይህ ሊኾን ግድ ነውና፡ ተጠንቀቁ! አትደንግጡ! ነገር ግን፡ ፍጻሜው ገና ነው፤ ሕዝብ፡ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም፡ በመንግሥት ላይ ይነሣሉ፤ በየሀገሩም፡ ረኃብ፥ ቸነፈርም፥ የምድር መናወጥም ይኾናል። እነዚህም ኹሉ፡ የምጥ ጣር መጀመሪያ ናቸው።" የሚለውንና በማቴዎስ ምሥራች፡ ምዕ. ፳፬፥ ቍ. ፬-፯ የተጻፈውን፡ የኢየሱስ ክርስቶስ መለኮታዊ ቃል፡ መርሕ ያደረገው እውነታ ነው።

ለዚህ እውነታ ማስረጃነት፡ በአገራችንና በየዓለሙ አህጉር በሰፈነው፡ የአስተዳደርና የፍትሕ ቀውስ፤ ምስቅልቅሉ በወጣው፡ ሙዓለ ንዋይና በጥቂቶች የሀብት ክምችት ምክንያት የተናጋውን፡ የዓለማውያኑን ኑሮ፥ በሥራ እጦትና በድኅነት ሥቃይ፥ በቀሣፊ ደዌያትና ባጓጉል ሕክምና መዘዝ፥ በጦር መሣሪያ ባለመብትነትና በሃይማኖት ሽብርተኞች የጀብደኝነት ድርጊት መነሻነት፡ እርስ በርስ የመተላለቁንና የጦርነቱን ማዕበል መስፋፋት፥ የረሃቡን ጠንቅና የቸነፈሩን መዓት፥ የድርቅ ጅራፍንና የመሬት መናወጥን፥ ደምሳሽ የኾኑትን፡ የዐውሎ ነፋስንና የውኃ ሙላትን፥ ሰደድ እሳትንና የምድር መደርባትን መዓት፥ በተለይም፡ ሕዝብ፡ በሕዝብ ላይ፥ መንግሥትም፡ በመንግሥት ላይ የመነሣሣቱ ነውጥ፥ በመጨረሻም፡ በአምልኮ ባዕድና በክፉት መንፈስ መስፋፋት ረገድ፡ እየጨመረና እየተባባሰ፥ እየከበደና እየተወሳሰበ የኼደውን እጅግ አሳዛኝ ኹኔታ፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ ይበቃል።

እነዚህን የመሰሉት፡ የተፈጥሮና ሰው-ሠራሽ ኃይላት መቅሠፍቶች መበርከት፥ ጠቅላላውን፡ የሰውን ልጆች ሥጋዊና ነፍሳዊ፥ መንፈሳዊና ኹለንተናዊም ጽኑ ችግር አስተውሎ በማገናዘብ፡ ይህን እውነታ፡ ኹሉም በያለበት፡ በጠለቀና በመጠቀ፡ ሃይማኖታዊ አእምሮ፡ በቀላሉ ሊመለከተው ይቻለዋል።

## የሰላም ለኢትዮጵያ ጾም ውጤት።

የዚህ መልእክት ዓቢይ ግብ፡ እንዲህ በሚል አጭር ዐረፍተ ነገር ይጠቃለላል፦ "ሰላም ለኢትዮጵያ" የኅዋ ሰሌዳ ያቀረበውን ማሳሰቢያ በመቀበል፡ ባለፉት ዓመታት የፈጸምናቸው፡ የጳጉሜ ጾምና ጸሎት ምሕላዎቻችን፡ እንደማንኛዎቹም የጾመ ኢትዮጵያ ሱባኤዎቻችን፡ ያስገኙት ፍሬያማ ውጤት አለ።

ይኸውም፡ <u>"እውነተኛዋ የእግዚአብሔር ሰላም፡</u> የሰብአዊው ፍጥረት መጀመሪያ ከኾኑት፡ ከአዳምና ሔዋን ህልውና አንሥቶ፡ እስከዛሬ፥ ለዘለዓለምም፡ በቅዱሱ ኪዳን አማካይነት፡ ለሰው ልጆች ኹሉ ተሰጥታለች፤ ነገር ግን፡ ተጠብቃ የኖረችው፡ በኢትዮጵያውያንና በኢትዮጵያውያት ዘንድ ብቻ በመኾኑ፡ እኛ ልጆቻቸው፡ ይህን እውነታ፡ ለእየራሳችን አውቀን፥ ለሌሎችም ለማሳወቅ መቻላችን ነው።" በሚል አጭር ቃል ሊገለጽ ይቻላል።

እንግዴህ፡ እውነታው ይህ ከኾነ፡ "መልካም ፍሬ" ከተባለው፡ ከዚህ ብቅዓት የተደረሰው፡ እንዲሁ በከንቱ፥ ወይም፡ በቀላሉ ሳይኾን፡ <u>በእውነተኛ ንስሓ ጠርቶ ከተመራ ሃይማኖታዊ ምግባር</u> መኾኑ፡ በአጽንዖት ሊታወቅ ይገባል። ያም ሃይማኖታዊ ምግባር፡ ለአገራችንና ለሕዝቧ፥ እንዲሁም፡ በስደትና በልዩ ልዩ ምክንያት፡ በመላው ዓለም ለተበተነው ወገናችን፥ ለቀረውም ዓለም ጭምር፡ እውነተኛዪቱን የእግዚአብሔርን ሰላም ለማስገኘት ይበቃ ዘንድ፡ በቅድሚያ፡ ከየራሳችን ንጹሕ ልቦና የመነጨው ንስሓችን፡ በፈጣሪና በቅድስት እናቱ መንበር ፊት፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ አምልኮ መቅረብ እንዳለበትና እንደነበረበት፡ ያለጥርጥር ይታወቃል።

እንዲህ ካልኾነ በቀር ደግሞ: ይህን የመሰለው ሕያው ጸጋ: በሌላ ዘዴና መንገድ ከቶ ሊገኝ የሚቻል አይደለም:: አዎን! በዚያ ንስሓችን ላይ ተመሥርቶ የተካኼደውና የተፈጸመው: ጾምና ጸሎት÷ ምጽዋትና ስግደት: እነሆ: ያን: በየራሳችንና በአገራችን ላይ የታየውን: የመልካም ፍሬ ምርት: በእውን  አበርክቶ ለማቅረብ ተቻለው::

ይህን እውነታ በሚመለከት: ቀደም ብለውና በጊዜው ተላልፈው በነበሩት መልእክቶቻችን አማካይነት: ዘለዓለማውያን የኾኑ: አንዳንድ ቍምነገሮች: በተቻለ መጠን: ለኹሉ ተሠራጭተው እንደነበረ ይታወሳል።

እነዚያን ቍምነገሮች  የተመለከታቸውና የሰማቸው:  አስተዋዩ ኢትዮጵያዊ ወገን ኹሉ: የዚህን እውነታ ምንነት: በቀላሉ እንደተረዳው ሊታበል አይቻልም። አዎን! ይኸው ሃይማኖታዊ ምግባራችን: ለዚህ የአሸናፊነት ፍሬ የበቃው: የዛሬ ኹለት ሺህ አምስት ዓመት: በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጸደቀችውና በጸናችው: በእውነተኞዪቱ <u>የእግዚአብሔር ሰላም</u> ፍቱን መሣሪያነት መኾኑን ስንገልጽ: እጅግ ደስ እያለንና ይህን ላደረገ ፈጣሪያችን: የሚገባውን ምስጋናችንን እያቀረብን ነው::

የዚህች: የእግዚአብሔር ሰላም ፍቱን መሣሪያነት: በሃይማኖትም÷ በምግባርም የተረጋገጠው: በዚያ: በአዲስ ኪዳኑ: የምሕረት ዘመን መባቻ ነበር፤ ያም ዘመን: በዲያብሎስ አበጋዝነት በሚመራው: የሰዎች የክፋትና የጥፋት ኃይላት÷ በኃጢኣትና በሞትም ላይ: እርሷ: ለአንዴና ለመቼውም ጊዜ: የድል አድራጊነት ዘውድን የተቀዳጀችበት ምዕራፍ ነበር፤ ከዚያም ወዲህ: ይኸው የአሸናፊነት ህልውናዋ: በእውነተኞቹ የእግዚአብሔር ወገኖች ልቦና አማካይነት: የምድርን ኹለንተና አጥለቅልቆና በዓለም ሕዝቦች መካከል ሰፍኖና ገንኖ ይታያል::

ይኹን እንጂ: "ለኢትዮጵያ: ሰላምን: ለማስገኘት: በ'ሰላም ለኢትዮጵያ' የጎዋ ሰሌዳ አሳሳቢነት: ባለፉት ዓመታት የተካኼዱት የጳጒሜ አጽዋማትና ጸሎታት:  ለኢትዮጵያ: ሰላምን አስገኝተዋል!" የሚለው: ይህ: ከዚህ በላይ የተሰጠው መግለጫ: በዘመኑ "ሃይማኖት-የለሹ" ኢትዮጵያዊ ትውልድ ዘንድ: ግራ ሊያጋባና ተቀባይነትን ላያገኝ ይችላል።

በእርግጥ፡ “ሃይማኖት የለኝም!” ሊል በሚችል ሰብአዊ ፍጡር ዘንድ፥ ወይም፡ የሃይማኖት ጉድለት ባላቸው ዘንድ፡ ይህን የመሰለው፡ ግራ የመጋባትና የመጠራጠር ችግር መፈጠሩ እንደማይቀር ግልጽ ነው::

ያ፡ ግራ የገባውና የሚጠራጠረው ወገን፡ ለዚህ ግራ መጋባትና ጥርጣሬ የተዳረገው፡ በራሱ ፍላጎትና ምርጫ እንጂ፡ ያስገደደው፡ ሌላ፥ ወይም፡ የበላይ ኃይል፡ ኖሮበት አይደለም፤ ወይም፡ ይህን እውነታ የመቀበል ፍላጎት ኖሮት ቢኾን፡ ይህንኑ ምርጫ ለማድረግ፡ ሥልጣንና መብት፥ ችሎታም አጥቶ አይደለም:: የዚያ ወገን ባልደረባ የኾነው፡ እያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር፡ ለዚያ፡ ግራ ለሚያጋባውና ለሚያጠራጥረው፥ ደካማና እኩይ ለኾነውም፡ ለግራኛው የመንፈስ ኃይል፡ ራሱን አሳልፎ የሰጠው፡ በገዛ ፈቃዱ ነው።

እንዲህ፡ የሃይማኖት አልባነት አባዜ የተጠናወተው፥ ወይም፡ የሃይማኖት ጉድለት ያለበት ተጠራጣሪ (መናፍቅ) ኾኖ፡ ግራ የተጋባውና ወላዋይ የኾነው፡ አዎን! በራሱ ምርጫ ነው፤ ስለዚህ፡ እነሆ፡ **በውስጡም፥ በውጪውም፡ የእግዚአብሔርን ሰላም አጣ! ለጠንቀኛ ጽኑ ብኩንነትም ተጋልጦ፡ ለክፉው ፍዳ ሊዳረግ በቃ!** ከዚህ የተነሣም፡ ይኸው፡ ምድራዊና ሥጋዊ ኑሮውን፡ በሥቃይ የሚገፋ ኾነ!

ይህም ማለት፡ "ያ ሰው፡ እውነታውን አምኖ መቀበሉ ቀርቶ፡ ስለእግዚአብሔር ሰላም የምትናገረውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት ሰምቶና ተረድቶ፡ ለማወቅ እንኳ ፍላጎት፡ ጨርሶ የሌለው ፍጡር መኾኑን፡ ለራሱም፥ ለፈጣሪውም፥ ለሌላውም ፍጡር አረጋግጦ አሳየ!" ማለት ነው፤ በዚህ ግብሩም፡ የተፈጠረባትንና ባሕርዩ የኾነችውን፡ “ሕሊና” የምትባለውን፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ከራሱ ውስጥ ገላልጦ ለማወቅ፡ ሰብአዊ ፍላጎቱን ከማነሣሣት ይልቅ፡ ላልተፈጠረበት፡ የግራ ቢስነት ሓሰት፡ ራሱን ለማስገዛት መጣርን መፍቀዱንና መምረጡን፡ በግል አስተሳሰቡና በህልውናው አካኼድ፡ እነሆ፡ ራሱ መሰከረ::

ስለዚህ፡ እያንዳንዱ ሰው፡ ባለማወቅ ጨለማ ተውጦና በድንቍርና መረብ ተተብትቦ፥ በሓሰትም እሥራት ተቀፍድዶ መኖርን የመምረጥ፥ ያን ኑሮ ተቀብሎ፡ በዚያ አሳዛኝ ኹኔታ የመኖርም ዝንባሌው፡ ከመጀመሪያዎቹ ፍጡራን፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥቶ የነበረነው።

ያም ኹኔታ፡ ዛሬም ያለ እና ወደፊትም፡ እስከዓለም ፍጻሜ የሚቀጥል መኾኑ፡ ይኸው፡ በግልጽ ይታያል። የእግዚአብሔርን እውነት ለማወቅ አለመፈለጉና ወደዚያ ግብ ለመድረስ፡ ጥረቱ ቀርቶ፡ አንዳችም ዓይነት ሙከራን እንኳ አለማድረጉ፡ ከዚያ ፍላጎት አለመኖር የተነሣ መኾኑ የታወቀ ነው።

ይህ አቋሙ፡ ከላይ በተወሳው የሃይማኖት ጒድለትና የአላዋቂነት አስተሳሰብ የተመረዘውን፡ ራሱን፡ ሰብአዊዉን ፍጡር፡ የቱን ያህል እንደጎዳው፡ ለራሱ አረጋግጦ ለማስረዳት፡ የራሱ፡ የዛሬው፡ የሰው ልጅ አሳዛኝ ኹኔታ ይበቃል:: አዎን! ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ በፈጣሪ በኩል የተካኼደው፡ የእግዚአብሔርን እውነት፡ ገልጦ የማሳየቱና አግዝፎ የማሳወቁ ነገር፡ ምሥጢር ሳይኾን፡ ገሃድ ወጥቶ፡ በእውን የተከሠተውና የተፈጸመው፡ የዛሬ ኹለት ሺህ አምስት ዓመት መኾኑ፡ በታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን አማኞች ዘንድ፡ በሃይማኖት ተቀባይነትን አግኝቷል።

ይህም ማለት፡ ቀድሞ የነበረችውና ኋላ፡ በራሳቸው፡ በሰብአውያን ፍጡሮች የተሳሳተ የምርጫ ጠንቅ ምክንያት፡ ለበርካታ ሺህ ዓመታት ታጥታ የቆየችውን፡ ያቺኑ፡ አማናዊቷን የእግዚአብሔርን ሰላም፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይኾን፡ ለመላው ፍጥረተ ዓለምና ለሰው ዘር ኹሉ፡ መልሶ ለማስገኘት የተቻለ መኾኑ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ በይፋ የተገለጠበትና የተረጋገጠበት ጊዜ ማለት ነው:: ነገር ግን፡ አብዛኛው የሰው ወገን፡ ይህን ተጨባጭ የኾነ መለኮታዊ እውነታ በሚመለከት፡ ምንም ዓይነት ድርጊት እንዳልተፈጸመ፥ ምንም ዓይነት ኹኔታም እንዳልደረሰ፡ እንደፍሬ ቢስና እንደከንቱ ነገር ቆጥሮ፡ በንቀት ስለተወው፡ እነሆ፡ ሰብአዊው ችግርና ሥቃይ እየጨመረ ኼዶ፡ አኹን ካለበት ደረጃ ሊደርስ ችሏል::

አዎን! በመጀመሪያ፡ በሥጋቸው፡ ወንድና ሴት፥ በነፍሳቸው ደግሞ፡ በራሱ መልክ አድርጎ የፈጠራቸው፥ በመጨረሻም፡ በቅዱስ መንፈሱ፡ የልጅነትን ጸጋ ያቀዳጃቸው እግዚአብሔር፡ ከመለኮታዊ እውቀቱና እውነቱ፥ ፍቅሩና ደስታው ጋር፡ ሰላሙን ጭምር፡ ለእኒያ ለመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን፡ በምልዓትና በስፋት ሰጥቷቸው ነበር።

እነርሱ ግን፡ በሥጋ ወልደው ከሚያሳድጉ፡ ሰብአውያን ወላጆች ይልቅ፡ እጅግ በበለጠ ደግነትና ርኅራኄ፥ እንክብካቤና ምቾት የያዛቸውን፥ ያን የመሰለውን ፍጹም የሕይወት ጸጋና ሀብት ያጎናጸፋቸውን፡ የሚያውቁትን ፈጣሪያቸውን ትተው፡ የማያውቁትን፡ የክፋትና የሓሰት፥ የጥላቻና የጦርነት አባትና አበጋዝ የኾነውን ዲያብሎስን ተከተሉ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ያች፡ **የእግዚአብሔር** ሰላም፡ በሰው ልጆች ዘንድ፡ ከደረሰባትና ከሚደርስባት የፍላጎት ማጣትና የፈቃደኝነት ጉድለት የተነሣ፡ ከሌሎቹ የደግነት ባሕርያት ጋር አብራ፡ ከሰዎች ልቦና ታጣች፥ ተሠወረች። በእርሷ ፈንታ፡ የእርሷና የመሰሎቿ ደጋግ ባሕርያት ተቃራኒዎች የኾኑት፡ የክፋት ጠባያት፡ በሰዎች ልቦና ውስጥ ተተኩ፥ ሰፈኑ።

## የእግዚአብሔር ሰላም ምንድን ናት?

"ለመኾኑ፡ **የእግዚአብሔር** ሰላም ስንል ምን ማለታችን ነው? **የእግዚአብሔር** የተባለችው ሰላም፡ ምን ዓይነት ናት? ሌላ ሰላም፥ ወይም፡ ሌሎች ሰላሞች አሉን?" የሚል ጥያቄ፡ የእግዚአብሔርን እውነት በማያውቁና በማያምኑ ዘንድ መኖሩ አይቀርም፤ ሊጠየቅ የሚያስፈልግ፥ አጥጋቢ መልስ ሊስሰጠውም የሚቻል፡ ተገቢ ጥያቄ ነው።

መልሱም፡ እንዲህ በሚል አጭር ቃል የሚጠቃለል ይኾናል፦ **የእግዚአብሔር** ሰላም ስንል፡ ከፍጹሟ የእግዚአብሔር ፍቅር የምትመነጨውን፡ ጥንታዊቷንና ብቸኛዪቱን፥ ደጊቱንና መልካሚቱን፥ ንጹሒቱንና እውነተኛዪቱን ሰላም ማለታችን ነው፤ እርሷም፡ **"አነ ውእቱ፡ ፍኖተ ጽድቅ ወሕይወት፤ ...ወአንሰ፡ በእንተ ዝንቱ ተወለድኩ፤ ወእንበይነ ዝንቱ መጻእኩ፡ ውስተ ዓለም፥ ከመ እኩን ሰማዕተ በጽድቅ!"**

ማለትም፡ **"እኔ፡ የእውነት መንገድ፥ ሕይወትም ነኝ፤ ሰው ኾኜ የተወለድሁት፥ ወደዚህም ዓለም የመጣሁት፡ ስለእውነት ምስክር ልኾን ነው!"** ብሎ በተናገረው፡ በእግዚአብሔር ወልድ ሰው መኾን፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በዚህ ዓለም፡ በሰዎች መካከል፡ በሕያው ሰውነት ገዝፋ ታይታለች፤ ተመላልሳለች።

ይህችው የእግዚአብሔርዋ ሰላም፡ በመለኮታዊ ሰውነቱ የተገለጠችበት፡ የሰላሙ ንጉሥ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶና አድጎ፡ በዚህ ዓለም የተመላለሰበትን ሰብአዊና መለኮታዊ ተልእኮ እንደፈጸመ፡ የተናገራቸውን ሕያዋን ቃላት፡ እዚህ ላይ መጥቀሱ፡ እግዚአብሔር፡ ስለሰላም ምሥጢርና ስለምንነቷ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ ያደረገውንና የገለጠውን፡ ዕፁብ ድንቅ የኾነውን፡ መለኮታዊ ሥራውን፡ በእውን አረጋግጦ ያሳያል፤ እነዚህም፡-

፩ኛ፡ የሾህ አክሊሉን ተቀዳጅቶ፡ በመስቀል ዙፋኑ ላይ ከመቸንከሩ በፊት፡ **"እንካችሁ! ይህ ሥጋዬ ነው፤ ይህም ደሜ ነው፤ ኹላችሁም፡ ብሉት! ጠጡት! ስለብዙዎች፡ ለኃጢኣት ይቅርታ የሚስሠዋ፡ የአዲስ ኪዳን መሥዋዕት ነው!"** (ማቴ. ፳፮፥ ፳፮-፳፰፡፡)

፪ኛ፡ ራቁቱን ተቸንክሮ ሣለ፡ **"አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!"** (ሉቃ. ፳፫፥ ፴፬።)

፫ኛ፡ ከተቸነከረበት መስቀሉ ሳይወርድ፡ ነፍሱ፡ ከሥጋው ተለይታ፡ ዘለዓለማዊውን ነጻነት፡ ለሕያዋንና ለሙታን ነፍሳት ለማብሠር፡ ወደሲዖል ስትኼድ፥ ሥጋው ደግሞ፡ ወደመቃብር ወርዶ፡ ለሦስት መዓልትና ለሦስት ሌሊት፡ የሰንበትን ዕረፍት ካረፈ በኋላ፡ መለኮት የተዋሓዳቸው ሥጋውና ነፍሱ፡ እንደገና አንድ ኾነው፡ በትንሣኤ አካል ተነሥቶ፡ ደቀ መዛሙርቱ፡ በኀዘንና በቀቢጸ ተስፋ (ተስፋ በመቍረጥ)፥ በፍርሃትና በድንጋጤ ተውጠውና ተሰብስበው በነበሩት ቤት፡ በመካከላቸው ተገኝቶ፡ **"ሰላም ለእናንተ ይኹን!"** ብሎ ያስሰማቸው ቃሎቹ ናቸው፡፡ (ዮሐ. ፳፥ ፲፱።)

**የእግዚአብሔር ሰላም፡ እንግዴህ፡ ይህች ናት፡፡**

በእርሷ አንጻር ደግሞ፡ ማለትም፡ **የእግዚአብሔር** እንደኾነችው፡ እንደዚችው፡ **ሰላም፡** ማስመሰያ የኾኑ፡ የሰዎች፥ ወይም የዲያብሎስ፡ የምትሓት፥ ወይም፡ የሓሰት ሰላሞች አሉ፡፡

ስለእነዚህ፡ የሰላም ዓይነቶች፡ አስከፊ ምንነትና መራራ ፍሬነት፡ እዚህ ላይ፡ ብዙም ማተት፡ የሚያስፈልግ አይመስልም፤ ምክንያቱም፡ ከአዳምና ሔዋን ጊዜ አንሥቶ፡ በቃኤል ወገኖች እየተካኼደ ባለው፥ የአቤል ወገን በኾነው፡ በኖኅ ዘመን የደረሰውን የጥፋት ውኃም እንኳ ሊያሻሽለው ሳይችል ቀርቶ፡ እስከዛሬ በቀጠለው፡ የሰው ልጆች አስተሳሰብ፥ አኗኗርና ድርጊት፡ እነሆ፡ በገሃድ ስለሚታይና በግዘፍ ስለሚዳሰስ ነው፡፡

እነዚህን የመሰሉትን የሰላም ዓይነቶች፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት አንቀበላቸውም፤ እውቅናም አንሰጣቸውም::

እኛ አምነን፥ እውቅናም ሰጥተን የተቀበልናት፡ የእግዚአብሔር ሰላም፡ ይህች ናት፦ በጥንቱ የፍጥረት ዘመን፡ ለአዳምና ለሔዋን የተሰጠች ኾና ሣለች፥ ነገር ግን፡ ከእነርሱ በኋላ የተተኩት፡ "የሰው ልጆች" የተባሉት ዘሮቻቸው፡ እርሷን፡ ካለመፈለጋቸው የተነሣ፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ፡ ከእነርሱ ተለይታ፥ ይኹን እንጂ፡"የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት ዘሮቻቸው በኩል ስለተፈለገች፡ በእነርሱ ዘንድ ተወርሳ በመከበሩዋ፡ እነርሱን ጠብቃ የቆየችዋን ነው፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** የምንላት።

በመጨረሻውም ዘመን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "ሰላምየ አኀድግ ለክሙ፤ ወሰላመ አቡየ እሁበክሙ፤ አኮ፡ በከመ ይሁብ ዓለም፡ ዘእሁበክሙ አነ::"

ማለትም፡ "ሰላሜን እተውላችኋለሁ! የአባቴንም ሰላም እሰጣችኋለሁ! እኔ የምሰጣችሁ፡ ዓለም እንደሚሰጠው አይደለም::" ብሎ ተናግሮላት፡ ላልፈለጓትና ለተዉዋት፡ ለሰው ልጆች ሳይቀር፡ በጸጋ የተመለሰችውን፡ የእግዚአብሔርን ሰላም ነው፡ እኛ፡ የእግዚአብሔር ሰላም የምንላት:: (ዮሓ. ፲፬፥ ፳፯::)

መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ስለእግዚአብሔር ሰላም ምሥጢር ምንነት፡ ለይቶ፡ ይህን መለኮታዊ ቃል የተናገረው፡ ለእነማን እንደኾነ፡ አበክሮ ማወቅና መገንዘብ፥ አተኵሮ መመልከትም ያስፈልጋል፤ ይገባልም።

አዎን! "በምድር ላይ፡ ሰላምን ለማምጣት የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ሰይፍን እንጂ፡ ሰላምን ለማምጣት አልመጣሁም:: ሰውን፡ ከአባቱ፥ ሴት ልጅንም፡ ከእናቷ፥ ምራትንም፡ ከአማቷ እለያይ ዘንድ መጥቻለሁ፤ ለሰውም፡ ቤተሰቦቹ፡ ጠላቶች ይኾኑበታል:: ማንም፡ ወደእኔ የሚመጣ ቢኖር፡ አባቱንና እናቱን፥ ሚስቱንም፥ ልጆቹንም፥ ወንድሞቹንም፥ እኅቶቹንም፥ የራሱን ሕይወት እንኳ ሳይቀር ባይጠላ፡ ደቀ መዝሙሬ ሊኾን አይችልም::

"መስቀሉን የማይዝ፥ በኋላዬም የማይከተለኝ፡ ለእኔ ሊኾን አይገባውም፡፡ ነፍሱን የሚያገኝ፡ ያጠፋታል፤ ነፍሱንም፡ ስለእኔ የሚያጠፋ፡ ያገኛታል፡፡" ያለውን ሕያው መመሪያውን አምነውና ተከትለው ለፈጸሙት፡ ለቀደሙትና ዛሬም ለሚፈጽሙት አማኝና ታማኝ ወገኖቹ ነው። (ማቴ. ፲፥ ፴፰-፴፱፡፡ ሉቃ. ፲፬፥ ፳፮-፳፯፡፡)

እንግዴህ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** የእግዚአብሔር እንደኾኑት፡ እንደመንፈሱ፥ እንደመንግሥቱ፥ እንደእውነቱ፥ እንደእውቀቱ፥ እንደፍቅሩ፥ እንደሕይወቱ፥እንደብርሃኑና እንደትንሣኤው ኹሉ፡ **የምትገኘው የምትኖረው፥ የምትሰፍነውም፡ በሰው ልቦና ውስጥ ነው፡፡**

ስለዚህ፡ ከላይ፡ በመልእክታችን መግቢያ ጀምሮ እንደገለጽነው፡ አንድ ሰብአዊ ፍጡር፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖት ከሌለው፥ ወይም፡ የዚህ ሃይማኖት "ተከታይ ነኝ!" እያለ፡ ነገር ግን፡ በሃይማኖቱ ጐደሎነት ምክንያት፡ ተጠራጣሪ ከኾነ፡ በዚያ ሰው ልቦና ውስጥ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** ልትገኝ፥ ልትኖርና ልትሰፍን ከቶ አትችልም፤ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በዚያ ሰው ልቦና ውስጥ ከሌለች ደግሞ፡ ያ ሰው፡ በውስጡ፡ ለራሱ ብቻ ሳይኾን፡ ከውጭውና በውጭ ካሉት፡ የተፈጥሮ ወገኖቹ፥ የሥነ ፍጥረቱ አካል አባሎች ከኾኑት ፍጡራንም ጋር፡ እውነተኛዋን ሰላም አግኝቶ፡ በሰላም ሊኖር ከቶ አይቻለውም፡፡

ይህ ነው፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ችግር፡፡ በቀደሙት ወላጆቹና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን፡ የቅዱሱን ኪዳን ስምምነት አፍርሶና ክዶ፡ በዚያ፡ በተቀደሰው ቃል ኪዳን ላይ፥ በሃይማኖታውያኑ ምልክቶቹና በምግባራዊው ሥርዓቱ ላይ ጭምር፡ ግልጽ ዓመፅንና የአምልኮ ምንዝርናን፡ በገሃድ እያካኼደ ስላለ፡ በራሱ ልቦና ውስጥ ኾነ፡ በአገሩና በወገኑ፥ በመካከሉና እርስ በርሱም፡ እውነተኛዋን የእግዚአብሔርን ሰላም፡ በቅርብ፡ ሊዳስሳትና ሊያገኛት ቀርቶ፡ በሩቁም እንኳ፡ በተስፋ ሊያያት ከቶ አልተቻለውም፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ በአገር ውስጥም ኾነ፡ ከአገር ውጪ ያሉት፡ የኢትዮጵያ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና ወገኖች፡ በመካከላቸውና እርስ በርሳቸውም እንኳ ቢኾን፡ የእግዚአብሔርዋን ሰላም ሊያገኟት አልቻሉም።

ያ ቀርቶ፡ በሰብአዊው፥ ወይም፡ በሌላው፡ በባዕዱ ሰላም እንኳ መጠቀም አቅቷቸው፡ ይኸው፡ በመላው ዓለም ፊት፡ ሲወነጃጀሉና ሲካሰሱ፥ ሲተናነቁና ሲተላለቁ፥ በመለኮታዊው ቃል መሠረትም፡ "ልቅሶና ጥርስ ማፋጨት" በበዛበት፡ አሳዛኝና አሠቃቂ ኹኔታ ሲማቀቁ ይታያሉ።

እንዲያውም፡ ቀድሞ፡ በሥልጣን ላይ የቆዩት፡ የእነዚሁ የሦስቱም ቤቶች ወገኖች፡ ከየሥልጣናቸው ተባርረው እንዲሰደዱና እንዲወገዱ፥ በእነርሱ ቦታ ላይ ደግሞ፡ አዲሶቹ ተተክተው፡ እነዚያን፡ ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ባለሥልጣኖች ሲያሠቃዩ የኖሩትን፡ እንዲያሠቃዩ የሚያደርገው፡ የመለኮት የጽዋ አዳይነት፡ በማይቀረው የዳኝነቱና የቅጣቱ ግዳጅ አፈጻጸም ሥርዓት፡ እየቀጠለበት መኾኑን፡ ይኸው ትውልድ፡ በማስተዋል ሊመለከተው ጨርሶ እንዳልቻለ፡ እነሆ ይታያል።

ይህም ማለት፡ በቅድሚያ፡ "በእግዚአብሔር ሥርዓተ መንግሥት እየተመራሁ አስተዳድራለሁ!" ይል የነበረው፡ የአጼ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ፡ ሊያከብረውና ሊጠብቀው በሚገባው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖቱና ምግባሩ ላይ፡ በጨለማና በሥውር ሲፈጽም ከኖረው ክህደቱና ዓመፁ፥ ምንዝርናውም፡ "ደርግ" በተባለው "እግዚአብሔር የለም!" በሚል ባዕድ ፍልስፍና በሚመራ፡ ጨካኝና ግፈኛ ኃይል ከተጋለጠ በኋላ፡ ፍዳው ያመጣበትን ቅጣት፡ በዚሁ በደርግ እጅ ተቀብሎ ማለፉን መዘንጋት ነው።

በማከታተል ደግሞ፡ ራሱ ደርግ፡ ጽዋው ሲደርስ፡ እርሱም፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት ላይ የፈጸመው ክህደትና ዓመፅ፥ አመንዝራነቱም፡ ከቀደመው የባሰና በይፋ የተገለጸ ኾኖ ስለተገኘ፡ እርሱን በሚቀጣውና የእግዚአብሔር ሰላም በሌለው፡ በሌላ ተቃዋሚ ኃይል ከሥልጣኑ ተባርሮ፡ እነሆ፡ እርሱም በፋንታው፡ በሠፈረበት የፍዳ ቍና እየተሠፈረበት፡ ይኸው፡ እርሱ ካፈራው ትውልድ ጋር፡ ከእርሱ በበለጠ፥ በተራቀቀና በሰላ ሠይፍ ሲመተር፡ መገኘቱን አለማጤን ነው።

በመጨረሻም፡ አኹን በሥልጣን ላይ ያለው አገዛዝ፡ እንደደርግ ኹሉ፡ የቅዱሱ ኪዳን ተቃዋሚነቱን፡ በግብር ጭምር፡ በይፋ ገልጦና አሳውቆ፡ በማናለብኝነትና በዕብሪት በሚያካኼድበት ጊዜ፡ በቀንደኞቹ፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ክህነቱና የቤተ ምልክናው መሪዎች ላይ፡ በተከታታይ የደረሰው ድንገተኛ ቅሥፈት፡ መልእክቱ ምን፥ ለማንስ እንደኾነ አመዛዝኖ ለመረዳት የተሣነው መኾኑ ነው።

አስተዋይ ተመልካችን የሚያስገርም፡ አንድ ሌላ፡ ልዩ ነገር አለ፤ ይኸውም፡ የዛሬው ኢትዮጵያዊ ትውልድ፡ ይህ ኹሉ መዓት የወረደበትና አኹንም፡ እየወረደበት ያለው፡ በምን ምክንያት እንደኾነ፡ ጠንቁን ሊያውቅ አለመፈለጉ፥ ወይም፡ አለመቻሉ ነው:: ጠንቁ፡ በቅዱሱ ኪዳን ላይ ከፈጸመው፡ ከራሱ ክህደት፥ ዓመፅና አመንዝራነት የተነሣ መኾኑን ለመገንዘብ ቢችልም፡ በንስሓ በመመለስ ፈንታ፡ ከልጅ ወደልጅ ሲተላለፍ ከቆየው፡ ከቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታዊ ውርሱ ጋር እልህ ተጋብቶ፡ "እምቢ፡ አሻፈረኝ!" ማለትን፡ አውቆና ፈልጎ መምረጡ ነው::

እንግዴህ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** የሌለችበት ሰውነት፥ ቤተሰብና ኅብረተሰብ፥ አገርና ዓለም፡ የህልውናው ዕድል ፈንታ፡ ይህ በመኾኑ፡ እጅግ ያስተክዛል:: ከዚህ ይልቅ የበለጠ የሚያሳዝነው፡ "ዛሬ፡ በኢትዮጵያ ሰላም የለም!" የሚል፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ አባል የኾነ ግለሰብ ቢኖር፡ ያ ሰው፡ ይህን የሚለው፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በኢትዮጵያና በዓለሙም ላይ ሳትኖር ቀርታ ሳይኾን፡ **<u>በራሱ፡ በዚያ ግለሰብ ሰውነት ውስጥ ባለመኖርዋ ብቻ መኾኑን፡ ሊያውቅ አለመቻሉ እና አለመፈለጉ ነው።</u>**

አዎን! የዚያ ሰው፡ ሥጋዊውና ነፍሳዊው፥ መንፈሳዊዉም ኹለንተናው፡ በሁከት ማዕበል ፈጽሞ የተተለቀለቀው፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** በውስጡ እንድትኖር ካለማድረጉ፥ ወይም፡ ካለመፍቀዱ የተነሣ መኾኑን፡ ይኸው ሰው፡ ሊረዳ አልቻለም፤ እንዲያውም፡ ለእርሱ፡ ሰላሙን የነሣውና መከራ ሥቃዩን የሚያሳየው፡ ያ፡ በአገሩና በዓለሙ ላይ ሰፍኖ ያለው ኃይል፡ እርሱ ራሱ፡ በፈጣሪውና በቅድስት እናቱ ቅዱስ ኪዳን ላይ በፈጸመው ክህደት፥ ዓመፅና የአምልኮ ምንዝርና ምክንያት፡ የመጣበት የቅጣት ዋጋው መኾኑን፡ ሊገነዘብ አልቻለም::

በዚህ ኹሉ ጊዜ፥ ወይም፡ በእነዚህ ኹኔታዎች መነሻነት፡ **የእግዚአብሔር ሰላም፡** በኢትዮጵያና በምድር ላይ፥ ወይም፡ በዚያ ግለሰብ፥ ቤተሰብና ኅብረተሰብ አካባቢ፡ "የለችም!" ማለት አይደለም፤ **የእግዚአብሔር ሰላምማ፡ ቀድሞ፡ በፍጥረት መጀመሪያ፥ ኋላም፡ የዛሬ ኹለት ሺህ አምስት ዓመት ከባተው፡ ከመጨረሻው የምሕረትና የሕይወት ዘመን ወዲህ፡ በተረጋገጠው እውንነት አለች።**

ይህም እውነታ፡ ከላይ ቀደም ብሎ፡ በሚበቃ ተብራርቷል። ሊያያት፥ ሊያገኛትና ሊጠቀምባት ያልቻለው እኮ፡ እስካኹን ተዘፍቆ ከሚማቅቅበት የክህደት፥ የዓመፅና የምንዝርና ኃጢኣቱ፡ "በእውነተኛ ንስሓ አልመለስም!" ብሎ፡ ልቡናውን ያደነደነው፡ ይኼ፡ የዛሬው የኢትዮጵያ ትውልድ ነው።

እውነተኞቹና ታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትማ፡ በውስጣቸውም፥ በውጫቸውም፥ በመካከላቸውና ባካባቢያቸው፥ በቤተሰባቸውና በኅብረተሰባቸው፥ በአገራቸውና በዓለሙም ዘንድ፡ **የእግዚአብሔር ሰላም** ሰፍና፡ እነሆ እየኖሩባት ስለሚገኙ፡ ለእግዚአብሔርና ለቅድስት እናቱ፡ የክብር ምስጋናቸውን ከማቅረብ፥ ለዚህ ጸጋ ላልታደሉት ወገኖቻቸውና ለመላው ፍጥረተ ዓለም ከመጸለይ በስተቀር፡ ከፈጣሪያቸው የጎደለባቸው፡ አንዳችም ነገር ከቶ የለም።

ኢትዮጵያም፡ እንደሰዎች ድርጊት ሳይኾን፡ የቃል ኪዳን ፈጣሪዋና አምላኳ እንደሠራትና የቅዱሱ ኪዳን ታማኝ ልጆቿ ጸንተው በቆሙላት ይዞታዋ፡ ይኸው፡ የማይገሠሥ ማንነቷንና ስሟን እንደጠበቀች፡ ካልተከፋፈሉትና ካልተለያዩት ሕዝቦቿና ምድሩዋ ጋር፡ **በእግዚአብሔር ሰላም** ተጠብቃ ትገኛለች፤ አዎን! ይህን፡ ከሃዲውንና ዓመፀኛውን፥ አመንዝራውንም ትውልዷን፡ ቀጥቶና አስተምሮ፡ ወደንስሓ ይመልሰው ዘንድ፡ የተግሣፅና የፍዳ ሠይፍን አስታጥቃ፡ በሥልጣን ላይ ካስቀመጠችው ኃይል ጋር፡ ይኸው፡ በነጻነት ህልውናዋና በእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ መለኮታዊ አመራርዋንና አስተዳደርዋን፡ በበላይነትና በተጠናከረ ይዘት ቀጥላበታለች።

ይህች፡ የእኛ ኢትዮጵያ፡ ራሷ ቅድስት ድንግል ማርያም ስለኾነች፡ ዳር ድንበር ሳይከልላትና የሚወስናት ጽንፍ ሳይኖር፡ ይኸው፡ በሰማያት ሳይቀር፡ በመላው ፍጥረተ ዓለም ዘንድ ታውቃና በሕዝቦች ልቦና ውስጥ፡ በሃይማኖት ተመሥርታ፡ ከሚመለከው መለኮታዊ ልጇ ጋር፡ በእግዚአብሔር እናትነትና በመንግሥቱ ንግሥትነት ሰፍና፡ ስትወደስና ስትመሰገን ትኖራለች።

እንዲህ እንደመኾኗ፡ በዛሬው የመጨረሻው ዘመን፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ልጆቿ፡ ለአልጫው ዓለም፡ ጨው፥ ለጨለማውም ዓለም፡ መብራት ኾነው፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነትን፡ በመላው ዓለም፡ አብዝተውና አስፋፍተው ይዘሩትና ይናኙት ዘንድ፡ እነሆ፡ በምድር ላይ ባሉ አገሮች ኹሉ ተሠራጭተው እንዲኖሩ አሠማርታቸዋለች።

በዚህም ረቂቅ ምግባርዋ፡ የእግዚአብሔር መንግሥትነቷ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ እንዲሰፍን ማድረጓን እየቀጠለች ትገኛለች፡፡ ይህ ኹኔታ፡ ስለእግዚአብሔር ሰላም፥ እስካኹን ለተገለጠው እውነታ፡ ግዙፍ ማረጋገጫ መኾኑን ለመገንዘብ ደግሞ፡ ለማንኛውም እውነተኛ የእግዚአብሔር ምእመን፡ የሚሳነው አይኾንም።

## ጾመ ጳጒሜ፡፡

"ጾመ ፍልሰታ" ካበቃች በኋላ፡ ኹለት ሳምንቶችን፡ በሥጋዊውና መንፈሳዊው የፋሲካ ደስታና የሓሤት ድግሥ ቆይተን፡ "ጾመ ጳጒሜ"፥ ወይም፡ "የጳጒሜ ጾም" ተብላ፡ ከሌሎቹ፡ የዓመቱ አጽዋማታችን መካከል፡ አንዲቱ ኾና የምታስተናግደን ሰሞን ትቀበለናለች። እርሷም፡ በመስከረም ፩ ቀን ለሚውለው፡ ለታላቁ የዐውደ ዓመት በዓላችን፡ ሰሙነ ዋዜማ የኾነችው የዓመቱ መደምደሚያ ጾም ናት ።

ጳጒሜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ፡ ለጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስና ለእመቤታችን ድንግል ማርያም የልደታት ቀን፡ እንደጾመ ገሃድ፥ አዲሱንም ዓመተ ምሕረት፡ በንስሓ ተዘጋጅተው ሊሸጋገሩባት፡ ሰሙነ ሱባኤ ኾና፡ ስትጾም የኖረች በመኾኗ፡ ዛሬም፡ እኛ፡ የአኹኖቹ ልጆቻቸው፡ በዚሁ መልክ የምንመራባትና የምንገለገልባት፥ የምንጠቀምባትም ኾናልናለች።

አዎን! መስከረም ፩ ቀን፡ ክፉዉን ኹሉ፡ ካረጀው ዓመት ጋር፡ ከወዲሁ ጥለንና ትተን፥ አስወግደንና አጥድተንም፥ የእየራሳችንን ኹለንተና፡ ለመንፈስ ቅዱስ ማደሪያነት፡ በንስሓ አድሰን፥ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ከኢትዮጵያዊቷ ድንግል ማርያም በመወለዱ፡ የተገኘውን፡ ዘለዓለማዊዉን የምሕረት ዘመን፡ እንደአዲስ ተሸላሚ፡ የክብር ልብስና የሕይወት አክሊል ተቀብለን፡ የምንጐናጸፍባትና የምንቀዳጅባት፡ ቅድስት ዕለት ናት፡፡

ከዚህ የተነሣ፡ የጌታችንና የእመቤታችን የልደት በዓላት የሚውሉባትን፡ መስከረም ፩ ቀንን፡ እውነተኛና ተገቢ በኾነው፡ የአምልኮ መንፈስ ለማክበር፡ ነፍሳችንንና ሥጋችንን፥ መንፈሳችንንም፡ በሥጋ ወደሙ ቀድሰን፡ ሰውነታችንን፤ እንዲህ፤ ለቅዱሱ ኪዳን ሕይወት የምናበቃባት፥ በአገርነትና በመንግሥትነት፡ የነጻነት በዓሏን፡ በዚያች ዕለት ለምናከብርላት፡ "ኢትዮጵያ" ለተባለችው፡ እናቱና እናታችንም፡ "ዕንቊጣጣሽ! (እነሆ፡ ዕንቊ ለጣትሽ!)" ብለን፡ የደስታና የምስጋና ገጸ በረከትን የምናቀርብባት፥ እርስ በርሳችንም፡ የአበባ ነዶና ጒንጒን አዘጋጅተን፡ "የምሥራች! እንኳን አሸጋገረን! እንኳን አደረሰን!" እያልን፡ መልካም ምኞታችንን የምንለዋወጥባት፡ የተመረጠች፡ የእግዚአብሔር ቀን መኾኗን አውቀን፤ ከወዲሁ፤ ተገቢውን ዝግጅት ማድረግ ይገባናል።

በዚህ መልክ የምንዘጋጅባትንና ከአሮጌው ዓመት፡ ወደአዲሱ ዓመት የምንሸጋገርባትን፡ ይህችኑ ጳጒሜን፤ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ን ዑስ ሱባኤ አድርገን፤ እነሆ፤ በጾም፥ በጸሎትና በምጽዋት ልናሳልፋት፤ በጒጒት እንጠብቃታለን።

እንግዴህ፡ በዘንድሮዋ ጳጒሜ፡ እኛ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ይህችው፡ የእግዚአብሔር ሰላም ባስገኘችልን፡ ባልተቋረጠውና በማይነጥፈው፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ እንደተመላን ኾነን፡ ፈጣሪያችን፡ ይህችኑ፡ በቸርነቱና በቤዛነቱ ያጸናልንን ሰላማችንን፡ በበለጠ እንዲያጠናክርልን፥ ለሌሎች ወገኖቻችንም፡ ህልውናዋን፡ አስፍቶና አጒልቶ፡ እንዲያሳይልን፡ ሱባኤያችንን፡ በታደሰ መንፈሳዊ ኃይል አካኺደን ልናከናውነው ይገባናል፥ ያስፈልገናልም፡፡

ለዚህችው፡ ለዘንድሮዋ ጳጒሜ የ"ሰላም ለኢትዮጵያ" ሱባኤያችን የተዘጋጁት የጸምና የጸሎት ሥርዓታት፡ ያው፤ ባለፉት ዓመታት፡ ለጸመ ኢትዮጵያ ያደረግናቸውን ተከትለው የሚፈጸሙ መኾናቸውን ስንገልጽላችሁ፡ እነዚሁ፤ የጸምና የጸሎት ሥርዓታት፡ በዚሁ ጎዋ ሰሌዳችን ዋና ገጽና በሌሎቹ ተጣማጅ መድረኮቻችን ላይ ሠፍረው የሚገኙ መኾናቸውን እያሳሰብናችሁ ነው፡፡

ሱባኤያችንን፡ በዚህ መልክና ይዘት በምናካኺድበት ጊዜ፡ የቀደሙት ወላጆቻችን፡ ይህን የመሰለውን ሃይማኖታዊ ግዳጃቸውን ከግብ ለማድረስ፡ ከሚጠቀሙባቸው ሥርዓቶች መካከል፡ እዚህ ላይ፡ ተጨማሪ ይኾነን ዘንድ፡ የዜና መዋዕላችን መዝገብ ከሚያስታውሰን ዝክረ ነገር፡ አንዱን ብቻ፡ እንዲህ በሚል ቃል ልናወሳላችሁ እንወድዳለን፡-

"ቅዳሴ ማርያምና መዓዛ ቅዳሴ፡ ኹለቱም ቅዳሴያት፡ ከተደረሱበት ዘመን ጀምሮ፡ በዳግማዊ አጤ ምኒልክ ጊዜ እስከተከሠተው፡ 'የኅዳር በሽታ' ድረስ፡ በፍልሰታ ሱባኤ፡ ቅዳሴ ማርያም፥ በወርኀ ጽጌ ደግሞ፡ መዓዛ ቅዳሴ፡ ተመድበው፥ በሌሎቹ፡ የእመቤታችን በዓላት ግን፡ በየተራ፡ ይቀደሱ እንደነበረ፥ በተለይም፡ በአገራችን፡ መቅሠፍት፥ ወይም፡ አንዳንድ ብሔራዊ ችግር በሚደርስበት ወራት፡ ማለትም፡ ቸነፈር (ወረርሽኝ በሽታ)፥ ድርቅ፥ ረሃብ፥ ወይም ጦርነት በተነሣ ጊዜ፡ አብያተ ክርስቲያናት፡ ጾም ጸሎት እንዲያደርጉ ሲታዘዙ፡ "ምሕላ ያዙ! መዓዛ ቅዳሴን ቀድሱ!" እየተባለ፡ የምሕላው ጊዜ እስኪፈጸም ድረስ፡ መደዳውን የምትቀደሰው፡ መዓዛ ቅዳሴ ነበረች።"

በዚህ መሠረት፡ የፍልሰታ ለማርያምን የነሐሴ ሱባኤ፡ በያመቱ፡ በቅዳሴ ማርያም ጸሎት እንደምናሳልፋት ኹሉ፡ "ሰላም ለኢትዮጵያ" በሚል የተቀደሰ ዓላማ በምናካኺደው፡ በዘንድሮዋ ጻጉሜ፡ የሱባኤና የምሕላ ጸሎታችንም ውስጥ፡ መዓዛ ቅዳሴን፡ አንደኛዋ ጸሎታችን አድርገን እንድንጸልያት፡ በተጨማሪ እናሳስባችኋለን። የዚህችኑ፡ የመዓዛ ቅዳሴ መጽሓፍ፡ ግእዙ፡ ከኢትዮጵያኛ (ዐማርኛ) ትርጉሙ ጋር አብሮ የተካተተበትን፡ ባለ፲፬፡ (ዐሥራ አራት) ቅዳሴ ጥራዝ፡ ከቅዱሳት መጻሕፍት መሸጫ፡ ፈልጎ ማግኘትና ለይቶ ማወቅ ይቻላል።

"ቸሩ ፈጣሪያችን፡ ይህችን፡ የ፳፻፭ (የ፪ሺ፭) ዓመተ ምሕረት፡ የጳጉሜ ምሕላችንንና ሱባኤያችንን፡ እንዳለፈው ዓመት፡ በሰላም አስፈጽሞን፡ ለአዲሱ የ፳፻፮ኛው (ለኹለት ሺ ስድስተኛው) ዓመተ ምሕረት ዐውደ ዓመት በዓላችን፡ በደኅና ያድርሰን!" እያልን፡ መልካም ምኞታችንን፡ አስቀድመን እናቀርብላችኋለን።

\+ \+ \+